የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ
የፌደሬሽን ምክር ቤት

The House of Federation
of
The Federal Democratic Republic
of Ethiopia

ቁጥር ፌዴም/ፌሪ/5/308
No
ቀን 23/02/2011
Date

ለወ/ሮ ፋጡማ ሐምዱ

<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የምክር ቤቱን ውሳኔ ስለማሳወቅ</u>

እርስዎ የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ማቅረብዎ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም የፌዴሬሽን ምክር ቤት መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም በ5ኛ የፓርላማ ዘመን 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ ባቀረቡት የሕገ መንግስት ትርጉም አቤቱታ ላይ ከፌደራል ሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የቀረበውን የውሳኔ ሃሳብ ከተመለከተ በኋላ ጉዳዩ የሕገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልገው አይደለም በማለት የሰጠውን የውሳኔ ግልባጭ 6/ስድስት/ ገጽ ከዚህ መሸኛ ደብዳቤ ጋር አባሪ በማድረግ ሰጥተንዎታል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ኬሪያ ኢብራሂም አሊ
የፌዴሬሽን ም/ቤት አፈ-ጉባኤ

<u>ግልባጭ</u>

- ለፌደራል ሕገ መንግስት ጉደዮች አጣሪ ጉባኤ
  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለሕገ መንግስት ትርጉም እና የማንነት ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
  <u>በፌዴሬሽን ምክር ቤት</u>

ስልክ 223322 ፋክስ 242304 E-mail: holethiopia@gmail.com ፖ.ሣ.ቁ. 20212/1000 አዲስ አበባ
Tel. 242301/03 Fax 241208 Web Site: http://www.hofethiopia.gove.et P.O.Box Addis Ababa

# የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የፌዴሬሽን ምክር ቤት 5ኛ የፓርላማ ዘመን

## 4ኛ ዓመት 1ኛ መደበኛ ጉባዔ

መስከረም 29 ቀን 2011 ዓ.ም

አመልካች፡- ወ/ሮ ፋጡማ ሐምዱ

ተጠሪዎች፡- እነ አቶ ሁሴን ቱፋ (2 ሰዎች)

የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፌዴሬሽን ምክር ቤት አመልካች ያቀረቡትን የሕገ መንግስት ትርጉም ጥያቄ መርምሮ የሚከተለውን ሕገ መንግስታዊ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

**ውሳኔ**

ጉዳዩ ለሕገ መንግስት ትርጉም ምርመራ ሊቀርብ የቻለው አመልካች ግንቦት 4 ቀን 2008 ዓ.ም ለጉባኤው ፅፈው ባቀረቡት አቤቱታ መነሻነት ነው፡፡ ጉዳዩ ከጋብቻ ንብረት ክፍፍል ጋር በተያያዘ የተደረገ ክርክርን የተመለከተ ነው፡፡ ጉዳዩ የተጀመረው 2ኛ ተጠሪ ከሳሽ በመሆን በ1ኛ ተጠሪ ላይ ባቀረቡት የጋብቻ ንብረት ክፍፍል ክስ ሲሆን አመልካች 1ኛ ጣልቃ ገብ በመሆን፣ ሌላኛዋ ሚስት የሆኑት ወ/ሮ አረቤ ጉደቶ 2ኛ ጣልቃ ገብ በመሆን እንደዚሁም ሌላ አንድ ግለሰብ 3ኛ ጣልቃ ገብ በመሆን በሊሙና ቢሊቢሎ ወረዳ ፍ/ቤት በተደረገ ክርክር ነው፡፡

የቀረበለትን ክርክር በመጀመሪያ የተመለከተው የሊሙና ቢሊቢሎ ወረዳ ፍ/ቤት የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃ ከተመለከተ በኂላ አዋሣኛቸው ተጠቅሶ በተለያየ ቦታ ከሚገኙ በጥቅሉ 15½ /አስራ አምስት ተኩል/ ሄክታር መሬት ውስጥ አመልካች የግሌ ነው ሲሉ ክርክር ያቀረቡበትን 4 ሄክታር መሬት ከ1982 ዓ.ም በፊት ለአመልካች የተሰጠ እና በ1982 ዓ.ም በ1ኛ ተጠሪ ስም የተመዘገበ መሆኑን በማስረጃ መረጋገጡን በመጥቀስ ይህ 4 ሄክታር ይዞታ የአመልካች እና የ1ኛ ተጠሪ ነው ሲል ወስኗል፡፡

ቀሪው 11 ሄክታር መሬት በ1982 ዓ.ም በሕጋዊ መንገድ ተለክቶ ሲሰጥ ከ1ኛ ተጠሪ ጋር አመልካች እና 2ኛ ተጠሪ የነበሩ እና እየተጠቀሙበት የሚገኙ መሆኑን በምስክሮች ቃል እና ከወረዳው መሬት አስተዳደር ጽ/ቤት በተላከው ማስረጃ ማረጋገጡን በመጥቀስ ይዞታውን አመልካች፣ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪ ለ3 ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በመዝገቡ ላይ 2ኛ ጣልቃ ገብ የሆኑት ሌላኛዋ ሶስተኛ ሚስት ከ1992 ዓ.ም በኂላ መጥተው ከ11 ሄክታሩ ላይ ሊካፈሉ እንደማይችሉ በመጥቀስ ከ1ኛ ተጠሪ ድርሻ ላይ ይካፈሉ ሲል ወስኗል፡፡ በአከራካሪነት በቀረቡት